# ቀስተ ደመና

የሰላምና የወድማማችነት ድምፅ ሬድዮ ጋዜጣ

ቁጥር 1-3 ልዩ እትም መስከረም / ህዳር 1990

## ከአዘጋጅ ብዕር

መስከረም 1 ቀን 1990 ዓ ም ሥርጭቱን የጀመረው የቀስተ ደመና ሬዲዮ፤ የሰላምና የወንድማማችነት ድምፅ የአራት ወራት የአገልግሎት ግዜውን አጠናቅቆ አምስተኛ ውን ወር ሊይዝ ነው።

የቀስተ ደመና ሬዲዮ የሚያስተላልፋቸው ዜናዎች ፤ ትችቶችና ትንተናዎች ፤ ቃለ መጠይቆች ወዘተ በአየር ላይ ውለው ሳይጨበጡ እንደተበተኑ የትም እንዳይቀሩና በፅሁፍ ተቀርፀው ቢቀመጡ ለተደራሲው የሚሰ ጡት ጥቅም የላቀ ይሆናል ብለን በማሰ ብ ፤ ከወራት በፊት አንድ መፅሄት ለመጀመር አቅደን ጊዜ ጊዜን እየወለደ ዛሬ ላይ ደርሰናል።

ባለፉት አራት ወራት ቀስተ ደመና ሬዲዮ ያስተላለፉቸውን ትችቶችና አስተያየቶች በማቀናበር ይህንን ‘ልዩ እትም’ አዘጋጅተናል። የተለያዩ ለሃገራችን ወቅታዊ ጉዳዮችና ጥያቄዎች ቅድሚያ ትኩረት የሰጡት እነዚህ አስተያየቶች በርካታ ቁም ነገሮች ያስጨብጣሉ የሚል ዕምነት አለን።

የ ‘ቀስተ ደመና’ ጋዜጣ ከዚህ ልዩ እትም በኋላ በየግዜው እንደሚወጣ ልናበስር እንወዳለን።

መልካም ንባብ !

ቀስተ ደመና ሬዲዮ የሚተላለፍበት ፕሮግራም ገጽ.....................................19

* የኢሃደግን ጦር ጠማሽ አቋም ላለማገዝ...........
ሰላማዊውን የፖለቲካ ትግል አለማፍዘዝ......................................4

* የቡድን ውኸ‌ንብር ጠቃሚነቱ ለአምባገነኖች ብቻ ነው ................10

* ከፓሪሱ ጉባዔ ያልተቀሰመው ትምህርት..................................3

* ከዶላር ወይስ ከናቅፋ ከጽድቅ ወይስ ከኩነኔ....................9

* ለብቸኛው ልዕለ ኃያል የሚሳነው ነገር አለ ለካ ሄ ሄ.....13

* በነ ዶር ታዬ ላይ በሃሰ ት አልመሰክርም በማለት ራሳቸው በሃሰት የተወነጀሉት ....................15

* ከባሻገሩ ሽግግሩ እንዳያስቸግር..18

* ለነፃ ምርጫ አመች የኃይል ሚዛን መታገል አንገብጋቢ ጥያቄ ነው ..............................................6

አስተያየት፤ ትችት፤ ወዘተ ካላችሁ አድራሻችን እንደሚከተለው ነው፤
Radio Rainbow
c/o P.O.Box 140104
53056 Bonn , Germany . Fax : 0049 228 612381

GRAPECA ሰኢአቀ RAGPEHA
Groupe de Recherche et d'Action pour la pain en Ethiopie et dans la Corne de l' Afrique
Research and Action Group for peace in Ethiopia and the Horn of Africa
ሰላም ለኢትዮጵያና አፍሪካ ቀንድ የምርምርና የተግባር ቡድን

# ቀስተ ደመና ሬዲዮ

መስከረም 1 ቀን 1990 ዓ ም (ሴፕቴምበር 11/ 1997)

ሰላም ለኢትዮጵያና ለአፍሪካ ቀንድ የምርምርና የተግባር ቡድን በሃገርም ውስጥ ሆነ ከሃገር ውጭ በተሰማሩ አባላቱ ንቁ ተሳትፎ በሃገራችን ሰላምና ዴሞክራሲ እንዲሰፍኑ የተቻለውን አስተዋጽኦ ለማድረግ ሲጥር የቆየ ድርጅት ነው።

ቡድኑ የዛሬ ሰባት ዓመት ሲቋቋም ሃገራችን ኢህአዴግና ሻቢያ በአንድ በኩል ደርግ በሌላ በኩል በአስከፊ ጦርነቶች ተፋጠው ወገን እርስ በርስ የሚጨራረስበት የጦር ሜዳ ነበረች ። ቡድናችን ይዞ የተነሳው አላማ በሃገራችን ዴሞክራሲ አብቦ ፤ የህዝቦችዋ አንድነትና ወንድማማችነት ስር ሰዶ ፤ ማህበራዊ ፍትህ ሰፍኖ ዘላቂ ሰላም የሚገነባበት አማራጭ ፕሮግራም ለመንደፍና ለዚህም መሳካት ለመታገል ነበር ። የኢህአዴግ ኢትዮጵያን መቆጣጠር ከነዚህ ክቡርና የተቀደሱ ዓላማዎች አንዱንም አላስገኘልንም ። በመሆኑም ከዚያን ወቅት ጀምሮ ድርጅታችን በተለያዩ ዘዴዎች ለነዚህ አላማዎች ትግሉን ያለማሰለስ ቀጥልዋል ።

ቡድናችን እስካሁን ካከናወናቸው ዋና ዋና ተግባራት አንዱ የፓሪሱንና የአዲስ አበባውን የሰላምና እርቅ ጉባዔዎች ሃሳብ በመጠንሰስና እንዲሳኩም አስፈላጊውን የማተሪያል ድጋፍ በመሰ ብሰብ ጉባኤዎቹ በተሳካ ሁኔታ እንዲከናወኑ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጎን ተሰልፎ የተጫወተው ሚና ነው ።

የቀስተ ደመና ሬዲዮ ዋና ተልእኮ የፓሪሱና የአዲስ አበባ የሰላምና እርቅ ጉባኤዎች መንፈስ በአዲስ መልክ አንሰራርቶ በሃገራችን ለሰላምና ለዴሞክራሲ የሚደረገው የፖለቲካ ትግል መልሶ ፈር እንዲይዝ ማድረግ ነው።

የፈጀውን ጊዜ ቢፈጅና የጠየቀውን መስዋእትነት ቢጠይቅ የኢትዮጵያ ችግሮች የሚፈቱት በነፃ ምርጫና በዚህም ምርጫ አማካኝነት በተሰየመ ጉባኤ በተነደፈ ዴሞክራሲያዊ ህገ መንግሥት ብቻ ነው።

በዚህ የረጂም ጊዜ የትግል ጉዞ ሁሉም ከወዲሁ ሊገነዘባቸው የሚገባው አንዳንድ መሠረታዊ ሃቆች አሉ። ዴሞክራሲ በቅድሚያ ባልሰፈነባቸውና በተለይም ደግሞ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ለነፃ ምርጫ ቅድመ መብቶች ብሎ ያሰፈራቸው ሰብአዊ መብቶች በሌሉበት ሁኔታ ከተካሄዱ ምርጭዎች መቼም ቢሆን የትም ቢሆን ይበልጥ ዴሞክራሲ ፈልቆ አያውቅም ። ከወዲሁ በተጨባጭ ያልተረጋገጡ የሕዝብ መብቶች በአሸበረቁ አንቀጾች በህገ መንጊሥት ላይ ስለሰፈሩ ብቻ እውን የሚሆኑበት ምንም ዘዴ የለም።

ምርጫዎች በርግጥ ነጻ እንዲሆኑ የህገ መንግሥት አንቀጾች ተከብረው አንድ ህብረተሰብ በህግ የበላይነት እንዲተዳደር ከወዲሁ በህዝባዊ ትግል ለዲሞክራሲ የሚያደላ የሃይል ሚዛን መፍጠር ያስፈልጋል። ይህንን አወንታዊ የኀይል ሚዛን ከምርጫና ከህገመንጊሥት መጠበቅ የዋህነትን ብቻ ሳይሆን ካለፉት 70 ዓመታት የሃገራችን የምርጫና የህገመንግሥት መራራ ፊዞች ትምህርት አለመቅሰምን ያመልክታል።

ይህ የኃይል ሚዛን በአንድ አፍታ ወይም በአንድ ጥያቄ ዙሪያ በሚደረግ ትግል የሚገኝ አይደለም ። የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ፥መሬት ላራሹ ፥ ብሎ የረጂም ግዜ የትግል ዓላማውን ካስቀመጠ በኋላ ለዚህ ታላቅ አዋጅ ሁኔታውን ማመቻቸት የቻለው በየስብሰ ባው ፤ በየሰልፉ ፤ በየመግለጫው ሁሉ ይህንን ጥያቄ እያነሳ አልነበረም። በሃገሪቱ የነበረውን የኃይል ሚዛን መቀየር የቻለው በየግዜውና በተሰበጣጠሩ ምክንያቶች ሰልፍ እየወጣ ፤ ተቃውሞውን እያሰማ፤ ህዝቡን እያንቀሳቅሰ ፤ አስከፊውን የፊውዳል ሥርዓት በማዋከብና በመገዝገዝ እንደነበረ ግልጽ ነው።

ዛሬም ቢሆን ወደዘላቂ አላማችንና ወደ ዘላቂ ሰላም በሚደረገው ጉዞ የሃገሪቱ ደሞክራቶች አመቺ የሆነ የሃይል ሚዛን መፍጠር የሚችሉት ህዝባችንን አስጨንቀው ከያዙት የመብት ፤ የህልውናና የኑስቁልና ኑሮ ችግሮች አንጻር ለእለት ከእለት ለሚያካሂደው የትግል አቅጣጫ እያሳዩ በነዚህ ጥያቄዎች ዙሪያ እየታገሉ ሰያታግሉት ብቻ ነው። ይህም ማለት ፤

<u>አንደኛ</u> ኢህአዴግ በሃገራችን ላይ የጫነው የወስላቶች ዴሞክራሲ ተጋልጦ የህዝብ አለኝታ የሆነ ስርዓት እንዲነግሥ ለዲሞክራሲ ፤ ለሰው ልጅ መብት በተጨባጭ ጥያቄዎች ዙሪያ ቀስ በቀስ እየተጠራቀመና እየተጠናከረ የሚሄድ የእለት ከእለት ትግል ማክያሄድ

ያስፈልጋል። ጥቂት አምባገነኖች በየእለቱ ዜጎችን በማፈን ፤ በጠራራ ፀሃይ አውራ ጎዳና ላይ በመረሸን ፤ በግፍና በገፍ በማሰር ፤ በህገ ወጥ ዘዴዎች ከሥራ በማባረርና በመሳሰሉት የግፍ ድርጊቶች በየእለቱ ህብረተሰቡን በማዋከብ ላይ ናቸው። ግፍ በተፈጸመ ቁጥር ፤ መብት በተረገጠ ቁጥር ሁሉም ያገባኛል ብሎ መነሳትና ግፈኞችን ማዋከብ ያስፈልጋል።

ሁለተኛ በብሄሮች ጥያቄና በኢትዮጵያ አንድነት ጉዳይም እንደዚሁ የብሄሮች እኩልነት የሃገርአንድነት ከሚሉ አጠቃላይ አቋሞች ዘልቆ መሄድ ያስፈስልጋል ። ስመ ጥሩው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ በሁለተኛ ደረጃ አስቀምጦት የነበረው የብሄር ጥያቄ ዛሬ በአስከፊና በከፋፋይ መልኩ አይሎ ፤ የጥላቻና የከፋፍለህ ግዛ ፖለቲካ በመንግሥት ደረጃ በጀት ተደዞለት ሃጋራችንን ወደ ጥፋት ይዞ ሊነጉድበት የሚችልበት ደረጃ ላይ ደርሰናል። የኢትዮጵያ ዴሞክራቶች ዴሞክሪያስያዊ መፍትሄ ሊሹለት በግንባር ቀደምነት ያነሱት ጥያቄ ዛሬ አክራሪዎች የስልጣን ጥማቸውን ለማርካት ጠልፈውት የሚመጻደቁበት ጥያቄ ሆኗል ። በዚህም የተነሳ ስውል ሲያድር የኢትዮጵያን ህዝቦች የአንድነትና የወንድማማችነት መንፈስ ሊበክሉ የሚችሉ ችግሮች በየእለቱና በየአካባቢው ሲከሰቱ እናያለን ። ከየብሄሩ የተውጣጡ ዴሞክራቶች በጋራ እየተወያዩ አንድ የጋራ ራዕይ መድረስ ብቻ ሳይሆን በተጨባጭ ለሚቀርቡ ችግሮች ዴሞክራስያዊ መፍትሄዎች መጠቆምና ለነዚህ መፍትሄዎች ተግባራዊነት ሲባል አክራሪዎችን ህዝቡ እንዲታገላቸው ካላደረጉ ለኢትዮጵያ ሰላምና ዴሞክራሲ ምንም የረባ አስተዋጽኦ እንደማያደርጉ ግልጽ ነው።

ሶስተኛ ለማህበራዊ ፍትህ መደረግ ያለበት እጅግ ሰፊ የትግል መስክ አለ። እገሌ ተገሌ ሳይባል የሃገሪቱ ተቃዋሚ ድርጅቶች በሙሉ ከህዝቡ የእለት ከእለት የመብት፤ የህልውና፤ የኑሮ ችግሮችና ትግሎች ርቀው በአየር ላይ በመንሳፈፍ ላይ የሚገኙት ኢህአደግ በፈጠረው ግርግር ይህንን ቁልፍ ጥያቄ ችላ በማለታቸው እንደሆነ ግልጽ ነው።

ዛሬ እጅግ ስግብግብና ደራሽ የሆኑ የወያኔ ባለሃብቶች በዚህ ለብዙሃኑ ገሃነም ባደረጓት አገራችን የገነት ደሴቶች እየገነቡ ናቸው። ይች ሃገር በታሪኳ አይታም ሰምታም በማታውቀው ሁኔታ ለጥቂቶች ቅጥ ያጣ መንደላቀቅ በየእለቱ ከፋቱ እየጨመረ በሚሄድ የድህነት፤ የመራቆትና የጉስቁልና አዘቅት ውስጥ እየወደቀች በመሄድ ላይ ነች።

ድሃው የኢትዮጵያ ገበሬ ራሱንና አንድ ለጋ ታጋይ ትውልድ ሰውቶ የመሬት ላራሹን ድል ከተጎናጸፈ በኋላ ደርግ ምርቱን ሊቀማው እንደሞከረ ሁሉ ዛሬ ደግሞ ኢህአደግ እስከናካቴው ከመሬቱ እየነቀለ ለጅብ ሲሰጠው እናያለን። ጉልት ቸርቻሪዋ ነጋዴ አንድ የወያኔ ባለሃብት ለአንድ ምሽት የሚረጨው ሃብት ለዓመት ገቢ በዛብሽ ተብላ በቤት ክራይ ጭማሪ ሳብያ ጉሮሮዋ እንዲዘጋ እየተደረገ ነው። ወዛደሩ በገዛ ሃገሩ ሰርቶ ለመኖር ያለው መሰረታዊ መብት ተነፍጎት ልጆቹ ለረሃብና ለእርዛት እየተዳረጉ ይገኛሉ። ምሁሩ በሰበብ አስባቡ ከስራው እየተፈናቀለ ለስደት ወይም በሃገር ውስጥ ለውርደት ኑሮ እየተጋለጠ ነው። በወጣቱ ትውልድ አካባቢ የተስፋፋው ስራ እጥነት ያልዳሰሰው ቤተሰብ ባለመኖሩ በአዲስ አበባ ከተማ እንኳን ከ 600ሺ በላይ የሚሆን የሥራ ኃይል ለራሱም ለሃገሩም ሳይጠቅም እንዲባክንና ጠውልጎ እንዲተን እየተደረገ ነው ።

ይህንን እያፈጠጠና እያገጠጠ የመጣ የማህበራዊ ፍትህ ጥያቄ ከህዝቡ ጎን ተሰልፈውና ታግለው መፍትሄ እስካልፈለጉለት ድረስ የተቃዋሚ ኃይሎችና የዴሞክራሲያዊ ትግል ጉዳይ እስካሁን እንደታየው ሚዳቆ በዚህ ቅምዝምዝ በዚያ እንደሆነ እንደሚቀጥል ለመተንበይ እጅግም አስቸጋሪ አይሆንም።

የኢትዮጵያችን ችግሮች መሰረታዊ ምንጫቸው ወያኔ የተከለው ግፈኛና ኢፍትሃዊ አገዛዝ ነው። ይህ አገዛዝ በህብረተሰቡ በፈጠራቸው ከአሸዋ የበዙ ችግሮች የተነሳም በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች በያለበትና በየለቱ እጅግ አስቸጋሪና የአልሞት ባይ ተጋዳይ ትንንቅ እያካሄዱ ናቸው። ይህ በየእለቱ በአይናችን ሥር በግብታዊነት እየተካሄደ ያለው ህዝባዊ የተከላካይነት ተጋድሎ ሰብሳቢ የተደራጀና ግንባር ቀደም አመራር ተነፍጎት ከቀጠለ ሃገራችንን የሚጠብቃት ችግር ከወዲሁ መገመት አስቸጋሪ አይደለም። በመሆኑም የሃገራችን ዴሞክራቶች አንድነታቸውን አጠንክረው ሲቻል በይፋ ስይቻል ደግሞ በህቡዕ ተደራጅተው ለዲሞክራሲ ፤ ለህዝቦች ወንድማማችነትና ለማህበራዊ ፍትህ ለሚደረገው ህዝባዊ ትንንቅ ግንባር ቀደም አመራር ለምስጠት ዝግጁ መሆን ይጠበቅባቸዋል///